# ታቦት ፤ ጽላት

የሰው ልጆች ተጨባጭ የሆነ ሕሊናቸው የሚያርፍበት ቁሣዊ ነገር መፈለግ እግዚአብሔር መንፈሱንና ክብሩን በሚታዩና በሚጨበጡ ነገሮች ላይ እንዲገልጽ አድርጎታል። እግዚአብሔርን በማምለክ ከመላው ዓለም ቀደምትነት ያላቸው እስራኤላውያኖች እግዚአብሔር ቃል በቃል እያንጋገራቸው ታላላቅ ተዓምራት እየሠራ መኖሩን ቢገልጽላቸውም እነርሱ ግን ሌሎች ባእዳን አማልክትን ከማምለክ ወደኋላ አላሉም ነበር። ከእብሪታቸው የተነሣ በቃል ብቻ የሚያንጋግረን አምላክ አንኾም የምናያቸው በመሃከላችን የሚመላለሱ አማልክትን ሰሩልን እያሉ መሪዎቻቸውን ያስቸግሩ እንደነበርና ጣእታትም ሠርተው ከግብጽ ባርነት ያወጣቸውን በአማልክት መካከል እንዳንተ ማን አለ? ብለው የመሰከሩለት አምላካቸውን በጣእት ለውጠው የሠሩላቸውን ጣእታት አምላኮቻችን ናችሁ አሉ።

በዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ከምድረ ግብፅ ወጥተው ማርና ወተት ታፈሣለች ወደምትባለው ተስፋይቱ ምድር ከነዓን ለመግባት በጉዞ ላይ እያሉ በሙሴ አማካይነት የቃል ኪዳኑና የመታዘዝ ምልክት የሚሆኑ አሥር ሕግጋትና ትእዛዛት የተጻፈባቸው ሁለት ጽላቶች ሰጠው። ለጽላቱም ማስቀመጫ የሚሆን ታቦት ከግራር እንጨት እንዲሠራ በእግዚአብሔር ታዘዘ ይህንንም አደረገ። ለታቦቱም ማደሪያ ቤተመቅደስን ሰሎሞን ሠራ ይህን ሁሉ በተራ እንመለከታለን።

**ጽላት ከእግዚአብሔር ስለመሰጠቱ**

ሀ. ኦሪት ዘጸአት 24 ፤ 12 "እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ በዚያም ሁን እነርሱን ታስተምር ዘንድ እኔ የጻፍሁን ትእዛዝ ከከበረ ድንጊያ የተሠራ ጽላት እሰጥሃለሁ አለው" እንግዲህ ጽላት ጣእት ነው ከተባለ ጣእትን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረጸው እግዚአብሔር ነው ማለታቸው አይደለምን? ታዲያ ከዚህ የበለጠ ክህደት ከየት ይገኛል።

ለ. ዘጸአት 31 ፤ 18 "እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸው ከከበረ ድንጋይ የተሰሩ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰበው።" እግዚአብሔር እሰጥሃለሁ ብሎም አልቀረ ለሙሴ ሰጠው።

ሐ. ዘጸአት 32 ፤ 15 – 17 "ሙሴም ተመለሰ ሁለቱንም የምሥክር ጽላቶች በእጁ ይዞ ከተራራው ወረደ ጽላቶቹም የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ። ጽሕፈቱም በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር።" ጽላት የእግዚአብሔር እንጂ የሰይጣን ገንዘብ አለመሆኑን ሲያስረዳን ጽላቶችም የእግዚአብሔር ሥራዎች ነበሩ ይለናል። ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ጽላት ይዞ ወደ እስራኤል ዘንድ ሲወርድ እስራኤል የጥጃውን ምሥል አቁመው ለእሱ ሲሰግዱ ተመለከታቸው። ከንዴቱ የተነሣ በእጁ የያዘውን የእንቁ ጽላት በጥጃው ሥእል ላይ ወረወረበት ጣእቱም ደቀቀ ጽላቱም ተሰበረ። ይህንን በመጥቀስ ለሙሴ የተሰጠው ጽላት ተሰብሯል እና ሌላ ጽላት አልሰጠውምና ከዚያ በኋላ ቀርቷል የሚሉ አሉ። ይህ ግን የእነርሱ ክህደት እንጂ እግዚአብሔር እንደፊተኞቹ ያሉ ጽላት እንዲሠራ አዞታል። ኪታች የምንጠቅሣቸው ጥቅሶች ማስረጃዎች ናቸው።

ሀ. ዘጸአት 34 ፤ 1 "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው ሁለት ጽላቶች እንደፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ በሰበርካቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩበትን እጽፍባቸዋለሁ"

www.ethiopianorthodox.org

ለ. ዘዳግም 10 ፥ 1 – 5 "በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ፊተኞቹ ያሉትን ሁለት የእብነበረድ ጽላቶች ጠርበህ ወደ እኔ ወደ ተራረው ውጣ" አለ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ማስረጃዎች የሰጠሁህን ጽላት ሰብረሃልና ከእንግዲህ ጽላት አያስፈልግህም የሚል ሃሣብ የያዙ ሆነው ተገኝተዋል? እያችሁ በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እታዳምጡ ያለው ጳውሎስ ለዚህ ነው።

ታቦት ማለት ትርጓሜው ማደሪያ ሲሆን ነገር ግን ለማደሪያነት ብቻ ሣይሆን መታያም መገለጫም ነበር። ንጉሥ በተፋን እንዲገኝ፤ እንዲገለጥ ታቦት የእስራኤል አምላክ መገለጫ ነው። ባጠቃላይ ታቦት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለምሕረት ለሕዝቡ በሚገለጽበት ጊዜ ዙፋኑ ነው።

<u>ታቦት የጽላት ማደሪያነቱ</u>

ዘዳግም 10 ፥ 1 – 5 ".... ለአንተም የእንጨት ታቦት ሥራ ከግራር እንጨትም ታቦትን ...ሠራ ጽላቶችንም በሠራሁት ታቦት ውስጥ አደረግኋቸው እግዚአብሔርም እንዳዘዘ በዚያ ኖሩ።" ታዲያ ታቦትን የሰይጣን መመለኪያ ጣኦት አድርገው የሚያዩ ሰዎች ምን ያህል እንደ ተሣሣቱ ተረድተው ይሆን? በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተሠራውን ታቦት ማንቋሸሽ እግዚአብሔርን መናቅ ማዋረድ ነው። እነዚህን ጥቅሶች ልብ ብለህ ተመልከታቸው። ዘጸ 25 ፥ 10–40 ፥ ዘጸ 37 ፥ 1–29 ፥ ዘጸ 26 ፥ 31 – 37

አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ሲሳለሙ የቤተ ክርስቲያንን ደጅ በእጃቸው እያሻሹ ፊታቸውን ሰውነታቸውን ሲደባብሱ ሲያዩ ይሣለቁባቸዋል። <u>ከመጽሐፍ ቅዱስም የወጡ ናቸው እያሉ ይተቻሉ። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን ያላነበቡና ያላወቁ እነሱ ሆነው እናገኛቸዋለን።</u> ዘጸአት 30 ፥ 22 – 38 ያለውን ስንመለከት እግዚአብሔር ለሙሴ ከተለያዩ ጥሩ ሽታና መዓዛ ካላቸው ነገሮች ቅዱስ ቅባት እንዲሠራ አዘዘው በዚያም ከመገናኛው ድንኳን ጀምሮ በውስጡ የሚገኙትን ንዋየ ቅዱሣት እንዲቀባና እንዲቀድስ ነገረው፤ እነሱንም የነካ ቅዱ<u>ስ እንዲሆን እግዚአብሔር በማይታበል ቃሉ ተናገረ። ይህም ሥርዓት ለትውልድ እንዲተላለፍና እንደማይቋረጥ ተናገረ።</u>

እንግዲህ በቅብአ ሜሮን የተቀደሰውን ቤተ ክርስቲያን ማሻሸት መሣም የሚቀድስ መሆኑን አውቀን አደረግነው እንጂ ባለማወቅ አላደረግነውም።

<u>ስለቤተመቅደስ</u>

ለጽላቱ ማደሪያ የሚሆን ታቦት እንደተሠራ ሁሉ ቤተ መቅደስ ደግሞ ለታቦቱ ማደሪያ ይሆን ዘንድ ተሠራ። በመጀመሪያ የመገናኛ ድንኳን ነበረ ይኸውም:–

በኦሪት ዘጸአት 33 ፥ 9 – 11 ባለው የተጠቀሰው ነው። ቀጥሎም ሰሎሞን ታላቁን ቤተ መቅደስ ሠራ 1ኛ ነገሥት 8 ፥ 1 – 66 ቤተመቅደስ ሠርቶ እንደጨረሰ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እግዚአብሔር ለዘለዓለም የሚኖርበት ማደሪያ ቤት መሠራቱን ተናገረ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ እንዲህም አለ። በፍጹም ልባቸው በፊትህ ለሚሄዱ ባሪያዎችህ ቃል ኪዳንንና ምሕረት የምትጠብቅ ብሎ ቃል ኪዳን ጠባቂነቱን ተናገረ። እንዲሁም የእግዚአብሔር ዓይኖች በቤተ መቅደስ እንደሆን ሰሙም በቤተ መቅደስ እንዲመሰገን። ሕዝቡ ሁሉ በዚህ ቤተ መቅደስ የሚጸልዩትን

www.ethiopianorthodox.org

ጸሎት እንዲቀበል በቤተ መቅደስ መጥተው ስለሃገር ስለግል ሕይወታቸው የሚያቀርቡትን ጸሎት እንዲሰማቸው ቃል አስገባው። እግዚአብሔርም በ፩ኛ ነገሥት 9 ፥ 1 – 9 ባለው ላይ ሰሎሞን ለጠየቀው ሁሉ የእሽታ መልስ መስጠቱን እናነባለን።

## ለታቦት ሊደረግ የሚገባ ክብር

ታቦት የእግዚአብሔር የክብሩ መግለጫ ዙፋን እንደሆኑ ሁሉ ይከበር ዘንድ ግድ ነው። ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት እናያለን።

–መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 4፥5 "የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ እስራኤል ሁሉ ታላቅ እልልታ አደረጉ"ምዕመናን ታቦት በሚወጣ ጊዜ እልልታ የሚያቀርቡት የሚያጨበጭቡት ይህን መሠረት አድርገው ነው።

–መጽሐፍ ሳሙኤል ካልዕ 6 ፥ 16 – 23 ዳዊት ለታቦተ ጽዮን የሚገባውን ክብር ሲያቀርብ ሜልኮል እንደናቀችው (እንደዛሬዎቹ መናፍቃን) እግዚአብሔር በሜልኮል ትዕቢት ተቆጥቶ ሜልኮልን መካን እንዳደረጋት ይገልጻል።

–ዘጸአት 3 ፥ 5 "ወደዚህ አትቅረብ አንተ ቀቆምክበት ሥፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ" ምዕመናን ቤተመቅደስ የተቀደሰች ስፍራ መሆንዋን ያምናሉና ወደተቀደሰችው ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጫማቸውን አውልቀው ነው ለሙሴ የተሰጠው ትዕዛዝ ምዕመናንን ሁሉ ይመለከታልና።

–መጽ ኢያሱ 5 ፥ 15 "አንተ የቆምክበት ስፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ" ሥጋውና ደሙ ከሚሠዋበት ስሙ ከሚጠራበት ከቤተ ክርስቲያን የበለጠ ቅዱስ ስፍራ በምድር ላይ የት ይገኝ ይሆን? ስለዚህ ክርስቲያኖች ለኢያሱ የተሰጠው ትእዛዝ እነሱንም እንደሚጠቀልል ያውቃሉና ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጫማቸውን ያወልቃሉ። በዚህም ትዕዛዝ እግዚአብሔርን ፈጻሚዎች መሆናቸውን ይመሰክራሉ።

–መጽ ኢያሱ 3 ፥ 3 "ሕዝቡን የአምላካችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ከስፍራችሁ ተነሥታችሁ ተከተሉት በእናንተና በታቦቱ ያለው ርቀት በስፍራ ሁለት ሺህ ክንድ ያህል ይሁን በዚህ መንገድ በፊት አልሄዳችሁበትምና የምትሄዱበትን መንገድ እንድታውቁ ወደ ታቦቱ አትቅረቡ ብለው አዘዙ" ይህ ሁሉ ሥርዓት ዛሬም በጥንታዊቱ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ይጠብቃል።

–ዘሌዋውያን 16 ፥ 2 "እኔ በሥርየት መክደኛው ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመጋረጃው ውስጥ በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ሥርየቱ መክደኛው ወደ ተቀደሰው ስፍራ ሁል ጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው" የእግዚአብሔርን ቤት እንደማንኛውም ቤት ያለምንም ዓላማ የምንወጣበት የምንገባበት የምንጨፍርበት አይደለምና ደግሞም ከጸሎት በስተቀር ዓላማዊ ድርጊቶች በፍጹም አይደረጉበትም።

–ዘሌዋውያን 26 ፥ 1 "እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ለእናንተ ጣኦት አታድርጉ የተቀረጸም ምስል ወይም ሐውልት አታቁሙ ትሰግዱለትም ዘንድ በምድራችሁ ላይ የተቀረጸ ድንጊያ አታኑሩ። ሰንበታቴን ጠብቁ መቅደሴንም ፍሩ"

www.ethiopianorthodox.org

የተቀረጸ ምስል የተባለው ሁሉ ታቦትን እንደማይመለከት ከላይ ያረጋገጥነው ነው። መቅደሴን
ም ፍሩ ብሎ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ እንኳን በመራመድ በመንቀጥቀጥ መሆን እንዳለበት ገለጸ
ልን።

ደግሞም ታቦትን ሲነኩ የሚገባቸው ካህናት ብቻ እንደሆኑ እግዚአብሔር በዖዛ ትምህርት ሰጥ
ቶናል። ዖዛ ሳይገባው የእግዚአብሔርን ታቦት ስለነካ እግዚአብሔር ቀሰፈው 1ኛ ሳሙኤል 6
፤ 6 – 7 ተመልከት። እኛም በድፍረት ሳይገባን የጌታን ታቦት ከነካን እንቀሰፋለን።
ይህ ሁሉ በብሉይ ኪዳን የነበረ ሥርዓትና አምልኮት ነው። በሐዲስ ኪዳን ግን ቀርቷል የሚሉ
አሉ። ይህም ለማስመሰል ለውን ለማሣሣት እንጂ በሐዲስ ኪዳንም ከላይ የጠቀስናቸው ሥርዓ
ታት ክርስቲያናዊ ሕግና ሥርዓት ሆነው እናገኛቸዋለን።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ክርስቲያን አገሮች በተለየ ሁኔታ የብ
ሉይ ኪዳን ሥርዓትና ሕግን ወደ ክርስትና ሕግና ሥርዓት ለውጣ ትጠቀምባታለች። ይህም ሊ
ሆን የቻለው ከቤተ ይሁዳ ቀጥሎ እግዚአብሔርን በመቀበል (በአምልኮተ እግዚአብሔር ውስጥ
በመግባት) ከሌሎች ሀገሮች ቀደምትነት ያላት ስለሆነ ነው ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ሕግና ስርዓ
ት አልፋለች። ከብሉይ ሕግና ሥርዓቶች ብዙዎቹን የወሰደች ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ
ጽላተ ኪዳን ታቦተ ሕግ ነው።

አዲስ ቤተክርስቲያን በሚሠራበት ጊዜ ከዕፅ ወይም ከእብነበረድ ተቀርጾ በላዩ የእግዚአብሔር
ምሥጢራዊ ስም (ሕቡዕ ስም) አልፋና ኦሜጋ ተጽፎ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀ
ብቶ በመንበሩ ይሠየማል። በቅዳሴም ጊዜ ሕብስቱና ወይኑ ወይኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ቆ
ሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ወይኑን ደም መለኮት ወደመሆ
ን የሚለውጠው በዚህ በታቦቱ ላይ ነው። ስለዚህ ከብሉይ ኪዳን ታቦት የሐዲስ ኪዳን ታቦት ለ
የት ያለ ነው። ያ ምሣሌያዊ ሲሆን ይህ ግን ጠማናዊ ነው።

የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእስ
ራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጽበት ዙፋን ነበር የሐዲስ ኪዳን ታቦት ግን የአምላክ ሥጋና ደ
ም የሚፈተትበት ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ ሥጋዬን ብሉ ደሜን
ጠጡ እያለ ያመኑትን ሁሉ የሚጠራበት የምሕረት መሰዊያ ነው። ክብርና ስግደትም የሚደረ
ግለት ስለዚህ ነው።

## እግዚአብሔር ቤተመቅደስን ባርኮ በሐዲስ ኪዳን እንደሰጠ የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

–ማቴ 5 ፤ 17 "እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ" ባለው አምላካዊ
ምስክርነት የኦሪት ሕግጋትና ስርዓት ሁሉም አለመሻራቸውን ልንጠቅስ እንወዳለን። የሻራቸ
ውን ሰዋዊ ስርዓቶች ራሱ በቅዱስ ወንጌል ገልጾልናል። ታቦት ግን ሕገ እግዚአብሔር እንጂ
ሰው በፈቃዱ የመሠረተው ሕግ ስላልሆነ አልተሻረም ምሣሌነቱ አማናዊ ሆነ እንጂ።

ቅዱስ ጳውሎስ እንኳን አይሁድን ላለማደናገር ሥርዓተ ኦሪትን ሲፈጽም ይታይ ነበር ለምሣሌ
በታናሽ እስያ ሲያስተምር በነበረበት ጊዜ ጢሞቴዎስ የተባለውን ወጣት ሲያስተከትል ሲጠራው
www.ethiopianorthodox.org
በዙሪያው ብዙ አይሁድ ስለነበሩ እንሱን ለማስደሰት ገዝሮ አስከትሎታል። የሐዋ. ሥራ 16 ፤
3 እሱም ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ በሕገ ኦሪት የተጻፈውን የብፅአት ሥርዓት ያደርስ ነበር። ለምሳ

ለምሳሌ በክንክራኦስ ስዕለቱን ለማድረስ ራሱን መላጨቱ የሚታወስ ነው። የሐዋርያት ሥራ 18 ፤ 18ይህም የኦሪት ስርዓት መሆኑን ለማወቅ ብንሻ ዘኁ. 6 ፤ 9 መመልከት ይቻላል።

ጌታ ራሱ ቤተ መቅደሱን አድሶ ባርኮ እንደሰጠን ሲያስረዳን በመቀደስ የሚገበያዩትን ሁሉ አስወጥቶ "ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት" ማቴ. 21 ፤ 12 – 13 ብሏል። የቤተ መቅደስ ማለፍ የተገለጸው ጌታ በመስቀል ላይ ሁሉ ነገር ተፈጸመ ብሎ በተናገረ ጊዜ ነው ያን ጊዜ የቤተመቅደስ መጋረጃ ለሁለት መቀደዱ ከእንግዲህ ወዲህ ቤተ መቅደስና በው ስጡ ያለው ስርዓት አያስፈልግም ማለቱ ነው ሲሉም ይሰማሉ።

በመሠረቱ ጌታ ተፈጸመ ያለው ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ስለኃጢያታችንም ተላልፎ ይሰጣል እኛን ከሰይጣን ባርነት ነጻ ለማውጣት እንደ ወንበዴ ተቆጥሮ ይሰቀላል ተብሎ የተነገረው የነቢያት ትንቢት ተፈጸመ ማለቱ ሲሆን የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት መከፈሉም ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ከታዩት ሰባት ተአምራት አንዱ ነው እንጂ አሁንም የቤተ መቅደስ ስርዓት ማለፍ የሚጠቁም አይደለም። እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ኦሪት ሥርዓት ሊጸልዩ ባልሄዱ ነበር፤ የሐዋርያት ሥራ 3 ፤ 1። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 6 ፤ 16 "ታቦትን በጣኦት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው" ብሎ ተቆርቋሪነቱን ለእግዚአብሔር ታቦት ባላሣየ ነበር።

–1ኛ ጢሞ. 3 ፤ 15 "... በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገቡ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ ቤቱም የእውነት አምድና መሠረት የሕያው የእግዚአብሔር ቤት ክርስቲያን ነው።"

እውን ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን እንኖር ዘንድ በጢሞቴዎስ ውክልና አሣወቀን ቤተ መቅደስ በሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተብሏል። ደግሞም ሰሎሞን በ1ኛ ነገሥት 18 ፤ 13 ላይ "እኔም ለዘላለም የምትኖርበት ማደሪያ ቤት በእውነት ሠራሁልህ እያለ እንዴት ተሸሯል ይባላል። እግዚአብሔርም የሰሎሞንን ልመና ሲያጸድቅለት" በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ ለዘለዓለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ "ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ።"1ኛ ነገሥት 7 ፤ 3 ብሎ የለምን? ይህን ቃል ኪዳኑን ሽሮ በሐዲስ ኪዳን ሕገ ኦሪት እንዳለ ተሸሯል እንዴት ይባላል? ይኸ እግዚአብሔርን ማስዋሸት አይሆንም? እርሱስ ክብርና ምስጋና ይግባውና የተናገረውን ቃሉን አያጥፍም። ዛሬም ቃሉን አክብሮ በቃሉ አለ። ቀድሶ የሰጠን ቤቱን ዛሬም እርሱ ይገኝበታል።

–ዕብ. 7 ፤ 1 – 14 የፊተኛይቱ ሥርዓት ከአሁኑ ሥርዓት ለየት ያለመሆኑ የብሉይ ኪዳኑ ሥርዓት ለአዲስ ኪዳኑ ሥርዓት እንደምሣሌ እንደነበር። አሁን ግን በአማናዊ ሥርዓት ውስጥ መሆናችንን ይገልጻል እንጂ የፊተኛው ሥርዓት ጭራሽ ተፍቋል አላለም።

–ራእይ 11 ፤ 1 – 15 "እንኳን በምድር በሰማይም የኪዳኑ ታቦት እንዳለ ይነግረናል።"

www.ethiopianorthodox.org
ዓምደ ሃይማኖት ከሚለው ብርሃኑ ጎበና ካሳተሙት የተወሰደ።